(አላህን በማመፁ ምክንያት) አላህ ያስቀመጠው የቅጣት ወሰን ካልሆነ በቀር (ስርአት ለማስያዝ) ተብሎ አንድም ሰው ከአስር አለንጋ በላይ እንዳይገረፍ።

ከአቡ ቡርዳህ አልአንሷሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: እርሱ የአላህን መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ሲሉ ሰማ፦ "(አላህን በማመፁ ምክንያት) አላህ ያስቀመጠው የቅጣት ወሰን
ካልሆነ በቀር (ስርአት ለማስያዝ) ተብሎ አንድም ሰው ከአስር አለንጋ በላይ እንዳይገረፍ።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) በወንጀል ላይ ካልሆነ በቀር አንድም ሰው ከአስር አለንጋ በላይ መገረፉን ከለከሉ። ሐዲሡ ውስጥ የተፈለገው በቁጥር ተገድበው ከአላህና ከመልክተኛው የመጡ ግርፋቶች ወይም ምቶች ወይም ልዩ ቅጣቶችን አይደለም። ይልቁንም በሐዲሡ የተፈለገው ስርአት ለማስያዝ ሲባል ሚስትንና ልጅን መግረፍ ቢያስፈልግ ከአስር አለንጋ አይጨምር ማለት ነው።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/2987